መልእክት ስድስት

**የተመለሱት ምርኮኞች መንጻት**
**ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- *ዕዝ.* 9፡1—10፡44፤ *ነህ.* 13፡23-30፤
*ማቴ.* 5፡8፤ *ራእ.* 21፡18፣ 21፤ 22፡4

**I. የጌታ ምለሳ ልዩና ብቸኛ ነው፣ ፈጽሞ ንጹሕ፣ ነጠላ እና ቅዱስ፣ ምንም ድብልቅ የሌለው መሆንም አለበት፣ ስለዚህ፣ የማንጻት ሥራን ለማከናወን ዕዝራዎች እና ነህምያዎች ያስፈልጉናል፤ በጌታ ምለሳ ደረጃዎች በሙሉ፣ የመንጻት አስፈላጊነት አለ፡-**

*ሀ.* "ቅዱሱ ዘር" አረማዊ ከሆነ ማንኛውም ነገር እንዲለይ በማድረግ ዕዝራ ምለሳውን አነጻ—*ዕዝ.* 9፡1—10፡44፡-

1. ዕዝራ ከመድረሱ በፊት፣ አንዳንድ እስራኤላውያን አረማዊ ሚስቶች ስላገቡና ከዚህ ድብልቅ ልጆች ስለወለዱ ድብልቅ ነበር፤ ይህ በቀጥታ ሳይሆን መንፈሳዊ በሆነ መልኩ ልንተገብረው የሚገባ ምሳሌ ነው።
2. በጌታ ምለሳ "ቅዱሱን ዘር" አረማዊ ከሆነ ማንኛውም ነገር ለመለየት የመንጻት አስፈላጊነት አለ—9፡1-2፡-
   *ሀ.* የጌታ ምለሳ ቅዱሱ ዘር ነው፤ ቅዱሱ ዘር አረማዊ ከሆነ ማንኛውም ነገር ጋር በፍጹም እንዳይዋሐድ በጣም ንጹሕ መሆን አለብን።
   *ለ.* ምለሳው ቅዱስ ሲሆን፣ የጌታን በረከት እናያለን—ሕዝ. 34፡26።

*ለ.* ከቤቱ ግንባታ በኋላ፣ መንጻት ያስፈልገናል (በዕዝራ አመራር እንደታየው)፣ ከከተማው መገንባት በኋላም፣ እንደገና መንጻት ያስፈልገናል (በነህምያ ፍጹምነት እንደታየው)—*ዕዝ.* 9፡1-2፤ 10፡1-44፤ *ነህ.* 13፡1-30።

*ሐ.* በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከሁሉም ድብልቅ ጥልቅ-ዝርዝር በሆነ መልኩ መንጻት አለብን፤ ማንኛውም ተራ ነገር እና ከጌታ ምለሳ ሰማያዊ ባሕርይ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ነገር መወገድ አለበት—2 ጢሞ. 2፡19-22።

**II. ባቢሎን የእግዚአብሔር ነገሮች ከጣዖታት ነገሮች ጋር ድብልቅ ነው፣ የባቢሎን መርህ የሰውን ነገሮች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር፣ የሥጋን ነገሮች ከመንፈስ ነገሮች ጋር የማደባለቅ መርህ ነው—2 ዜና 36፡6-7፤ *ዕዝ.* 1፡11፤ *ራእ.* 17፡3-5፡-**

*ሀ.* የባቢሎን ክፍል የሆነ ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር እይታ አስጸያፊ ነው፣ ባቢሎናዊ የሆነ ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማሸነፍ ለሰይጣን ስፍራ ይሰጠዋል—ኢያ. 7፡1-21።

*ለ.* እግዚአብሔር የባቢሎንን መርህ ከምንም ነገር በላይ ይጠላል፤ እኛም የባቢሎንን መርህ እንደምንጠላ መመስከር የምንችለው በውስጣችን ባለ ባቢሎናዊ በሆነ ነገር ሁሉ ላይ ስንፈርድ ብቻ ነው።

**III. በሐዋርያት ሥራ 21 እና በያዕቆብ መጽሐፍ፣ ድብልቅ አለ፤ ያዕቆብ ብሉይ ኪዳንን ከአዲስ ኪዳን ጋር፣ አዲሱን መግቦተ ዘመን ከአሮጌው ጋር፣ የእግዚአብሔርን አዲስ ሕዝብ ከአሮጌው ጋር፣ አዲሱን ሰው ከአሮጌው ሰው ጋር ደባልቋል—*ያዕ.* 1፡1፣ 17-18፤ 2፡1-4፣ 8-12፤ 3፡2፤ 4፡11-12፤ 5፡10-11፡-**

*ሀ.* የሐዋርያት ሥራ 21 በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን አሰቃቂ ድብልቅ ያጋልጣል፤ አይሁዳውያን አማኞች እስከአሁን የሙሴን ሕግ ጠብቀዋል፣ በብሉይ ኪዳን መግቦተ ዘመን ቀርተዋል፣ የእግዚአብሔርን አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ከአሮጌው የብሉይ ኪዳን ኢኮኖሚ ጋር በማደባለቅ ጠንካራ በሆነ መልኩ በይሁዲነት ተጽዕኖ ሥር ነበሩ—ቁ. 18-21።

*ለ.* የሕግ መግቦተ ዘመን ሙሉ በሙሉ እንዳበቃ፣ የጸጋ መግቦተ ዘመን ሙሉ በሙሉ መከበር እንዳለበት እና በእነዚህ ሁለት መግቦተ ዘመናት መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ ማንኛውም ቸልተኝነት የእግዚአብሔር መግቦተ ዘመናዊ አስተዳደር ተጻራሪ እንደሚሆን እና እንደ የክርስቶስ መገለጥ ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ለሆነው ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚያዊ ዕቅድ ታላቅ ጉዳት እንደሚሆን አላወቁም—ዮሐ. 1፡16-17፤ ራእ. 2፡9።

*ሐ.* ሕጉ እግዚአብሔር በሆነው ነገር መሠረት በሰው ላይ ጥያቄ ያቀርባል፤ ጸጋ እግዚአብሔር የሚጠይቀውን ለማሟላት እግዚአብሔር በሆነው ነገር ለሰው አቅርቦት ይሰጣል፤ ጸጋ ሰው እግዚአብሔርን ሲደሰተው ነው—ዮሐ. 1፡16-17፤ ገላ. 6፡18፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ 12፡9፤ 1 ጴጥ. 4፡10፤ ኤፌ. 3፡2፤ 4፡29፤ 6፡24።

**IV. በእግዚአብሔር ልጆች ዘንድ ያለው ታላቅ ችግር የእኔነት ከመንፈስ ጋር መደባለቅ ነው—*ዕብ.* 4፡12፡-**

*ሀ.* ይህ ድብልቅ እግዚአብሔርን ከማገልገል ብዙዎችን ውድቅ ያደርጋል፣ ምክንያቱም በመንፈሳቸው እግዚአብሔርን የማያስደስት ብዙ ድብልቅ አለና—2 ጢሞ. 1፡3።

ለ. በውስጠኛው ክፍላችን ውስጥ ያለው መንፈስ ንጹሕ እና ያልረከሰ ነው፤ ሆኖም ግን፣ መንፈስ ሲወጣ እና በነፍስ እና በሰውነት በኩል ሲያልፍ፣ በቆሻሻነት እና በብልሽት ሊበከል ይችላል—2 ቆሮ. 7፡1።

ሐ. መንፈስን ማስተካከል ንጹሕ ያልሆኑ አነሣሽ ምክንያቶችን እና ውጥኖችን እንዲሁም በውስጣችን ያሉ ሌሎች ድብልቆችን ማስወገድ ላይ አጽንዖት ይሰጣል—1 ተሰ. 5፡23፤ 2 ጢሞ. 1፡7።

## V. በልብ፣ በሕሊና እና በመንፈስ ንጹሐን መሆን ያስፈልገናል፦

ሀ. ልበ ንጹሐን እግዚአብሔርን ያዩታል—ማቴ. 5፡8፤ ኢዮ. 42፡5፤ ራእ. 22፡4፦

1. በልብ ንጹሕ መሆን በዓላማ ነጠላ መሆን፣ ለእግዚአብሔር ክብር የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመፈጸም ብቸኛ ግብ ያለው መሆን ነው—1 ቆሮ. 10፡31።
2. ንጹሕ ልብ ጌታን እንደ ልዩና ብቸኛ ግቡ የሚወስድ ልብ ነው—1 ጢሞ. 1፡5፤ 2 ጢሞ. 2፡22፤ መዝ. 73፡1።
3. በአዲስ ኪዳን አነጋገር፣ እግዚአብሔርን ማየት እግዚአብሔርን ማትረፍ ነው፣ እግዚአብሔር ማትረፍ በእግዚአብሔር እንቀናበር ዘንድ እግዚአብሔርን በንጥረ-ነገሩ፣ በሕይወቱ እና በባሕርይው መቀበል ነው፤ እግዚአብሔርን ማየት ይለውጠናል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔርን በማየት ንጥረ-ነገሩን ወደ ውስጣችን እንቀበላለን፣ አሮጌው ንጥረ-ነገራችንም ይወገዳል—2 ቆሮ. 3፡18።
4. እግዚአብሔርን በሕይወቱ እንድንገልጠውና በሥልጣኑ እንድንወክለው፣ እግዚአብሔርን ማየት አምላክ-ሰው ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ክቡር መልክ መለወጥ ነው—1 ዮሐ. 3፡1-3፤ ዘፍ. 1፡26።
5. ልበ ንጹሐን መሆን እና ለጌታ ምለሳ ነጠላ መሆን አለብን፤ ያኔ ብቻ ለጌታ ምለሳ እርዳታ እንሆናለን—1 ጢሞ. 1፡5፤ 2 ጢሞ. 2፡22፤ 1 ጴጥ. 1፡22።

ለ. በጎ ሕሊና ብቻ ሳይሆን ንጹሕ ሕሊናም ጭምር ያስፈልገናል—ሐዋ. 23፡1፤ 24፡16፤ 1 ጢሞ. 3፡9፤ 2 ጢሞ. 1፡3፦

1. በጎ ሕሊና በእግዚአብሔር እና በሰው ዘንድ ነውር የሌለበት ሕሊና ነው—ሐዋ. 23፡1፤ 24፡16።
2. ንጹሕ ሕሊና ከማንኛውም ድብልቅ የጠራ ሕሊና ነው፤ እንዲህ ያለው ሕሊና፣ እንደ ጳውሎስ፣ እግዚአብሔርን እና ፈቃዱን ብቻ እየፈለግን እንደሆነ ይመሰክራል—2 ጢሞ. 1፡3።

ሐ. በሥራው ውስጥ የመጀመሪያው መሥፈርት የመንፈስ ንጽሕና ነው—2 ቆሮ. 6፡4፣ 6፦

1. መንፈሱ ንጹሕ የሆነን ሰው ማግኘት ከባድ ነው (7፡1)፤ ንጹሕነት በአመራር ውስጥ ቅድመ ሁኔታ እና የአገልግሎታችን መሠረታዊ ሁኔታ ነው (1 ጢሞ. 3፡9፤ 1፡5)፤ የድብልቅ ችግር በሠራተኞች ዘንድ ያለው ታላቁ ችግር ነው፤ አብዛኛውን ጊዜ፣ ንጹሕ አለመሆን ያለመግባባት እና የጥርጣሬ ምንጭ ነው (2 ጢሞ. 1፡3፤ 1 ጢሞ. 3፡9፤ ቲቶ 1፡15)።
2. መንፈሳችን ሲለቀቅ አደገኛ ወይም ለሌሎች ችግር የሚፈጥር እንዳይሆን በመንፈሳችን ውስጥ ያለውን ድብልቅ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ያስፈልገናል።
3. እግዚአብሔር እንዲጠቀምብን ከፈለግን፣ መንፈሳችን መለቀቅ አለበት፣ መንፈሳችን ንጹሕ መሆንም አለበት—2 ቆሮ. 6፡4፣ 6።

## VI. የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማዋ ንጹሕ ወርቅ፣ እንደ ጠራ ብርጭቆ ነው፣ የከተማይቱም ጎዳና ንጹሕ ወርቅ፣ ብርሃን እንደሚያሳልፍ ብርጭቆ ነው—ራእ. 21፡18፤ 21፦

ሀ. ወርቅ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያመለክታል፤ ከተማይቱ ንጹሕ ወርቅ መሆኗ ከተማይቱ መለኮታዊውን ባሕርይ ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ የያዘች እና መለኮታዊውን ባሕርይ እንደ ንጥረ-ነገሯ የምትወስድ መሆኗን ያመለክታል—ቁ. 18።

ለ. የጎዳናዋ እና የከተማይቱ ንጹሕ ወርቅ እንደ የጠራ ብርጭቆ ነው፣ ይህም ከተማይቱ በሙሉ ብርሃን የምታሳልፍ እንጂ ብርሃን ከል (ብርሃን የማታሳልፍ) ፈጽሞ አለመሆኗን ያመለክታል—ቁ. 21፦

1. የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንደ ልዩና ብቸኛ መንገዳችን ከተከተልን፣ ንጹሐን፣ ምንም ዓይነት ድብልቅ የሌለብን እና ብርሃን የምናሳልፍ፣ ምንም ዓይነት ብርሃን ከልነት የሌለብን እንሆናለን።
2. ሕይወት-በሚሰጠው መንፈስ ከተሰረጽን እና ከተሞላን፣ የውስጡ ማንነታችን ብርሃን አሳላፊ እና እንደ ብርሌ የጠራ ይሆናል—2 ቆሮ. 3፡8-9፣ 18።

ሐ. እውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንዲኖረን ከፈለግን፣ ቤተ ክርስቲያን ራሷ ንጹሕ ወርቅ፣ ማለትም፣ ቅንብሯ ሙሉ በሙሉ መለኮታዊው ባሕርይ መሆን አለበት፤ እዚህ ጋር የመስቀሉ ሥራ ሊያነጻን እና ሊያጠራን ያስፈልገናል—ራእ. 1፡11፣ 20።

መ. በከሃዲው የክርስትና ዓለም እና በእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ልዩነት አንደኛው ድብልቅ መሆኑ፣ ሌላኛው ንጹሕ መሆኑ ነው፤ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ እንደ ብርሌ የጠሩ፣ ምንም ዓይነት ድብልቅ የሌለባቸው መሆን አለባቸው—22፡1።

*© 2022 Living Stream Ministry*